# 26ኛው የግንቦት ሃያ በዓል በቤጂንግ የኢፌዴሪ ኤምባሲ በድምቀት ተከበረ፣



26ኛው የግንቦት ሃያ የድል በዓል በቤጂንግ የኢፌዴሪ ኤምባሲ ቤጂንግና አካባቢው የሚገኙ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር አባላትና ደጋፊዎች፣ በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ የኢትዮጵያ ተማሪዎች፣ የኤምባሲው ሠራተኞችና ቤተሰቦቻቸው፣ እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው የኤምባሲው ወዳጆች በአጠቃላይ ከ200 በላይ ታዳሚዎች በተገኙበት ግንቦት 20 ቀን 2009 ዓ.ም ከቀኑ 11:00 ሰዓት ጀምሮ በግራንድ ሚሊኒየም ቤጂንግ ሆቴል “የህዝቦች እኩልነትና ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ያረጋገጠ ፌዴራላዊ ስርዓት እየገነባች ያለች ሀገር - ኢትዮጵያ” በሚል መሪ ቃል በፓናል ውይይት በድምቀት ተከብሯል፡፡



በፓናል ውይይቱ ላይ መነሻ ሃሳብ ያቀረቡት የህወሓት/ኢህአዴግ መሥራች ታጋይና በቻይና የኢፌዲሪ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር የሆኑት ክቡር አቶ ስዩም መስፍን ለዘመናት የተንሰራፋውን ጨቋኝ ሥርዓት ለመገርሰስ ከትውልድ ትውልድ እየተሸጋገረ የመጣውን የህዝብ ትግል በተደራጀ መልክ ለ17 ዓመታት በሙሉ በኢትዮጵያ በረሃዎችና ተራሮች ረጂም ትግል ተካሂዶ በግንቦት ሃያ ድል መደረጉን አውስተዋል፡፡ አያይዘውም የፌደራላዊ ሥርዓታችን የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መሠረታዊ መብቶቹን ያስከበረለት ነገር ግን ገና በጨቅላ ዕድመ ደረጃ የሚገኝ ሥርዓት በመሆኑ አደራ ተረካቢው ወጣቱ ትውልድ በቁርጠኝነት መጠበቅ እንደሚገባው መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡



ክቡር አምባሳደሩ አክለውም ባለፉት 26 ዓመታት ጉዞ ከድህነቱ ጋር በተደረገው ትግል የተመዘገቡት የልማት ውጤቶች ተስፋ ሰጪ መሆናቸውንና አገራችን ከሰሃራ በታች ካሉት አፍሪካ አገሮች መካከል ከግንባር ቀደሞቹ ለመመደብ መብቋቷን አንስተው፣ ይህንኑ ለማስቀጠል ሁሉም በየደረጃው በቁርጠኝነት የሚጠበቅበትን መወጣት እንዳለበት አሳስበዋል፡፡ በመጨረሻም ሻማ የማብራትና የኬካ ቆረሳ ሥነ-ሥርዓት በተሳታፊዎች የተካሄደ ሲሆን ምሽቱ በብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሙዚቃዎችና ጭፈራዎች የደመቀ ነበር፡፡